# <u>እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2018 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>


በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በስርጭት ከፍተኛ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ በፀሃይ ሀይል በመታገዝ ከሚፈጠረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት ከባድ መጠን ያለዉ እና ነጎድጓድ አዘል ዝናብ ይዘወተራል፡፡

ባለፉት ኦገስት የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመጠናከራቸዉ ምክንያት በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ሥፍራዎች ላይ የዝናቡ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋ ሲሆን፤ ከምስራቅ እና ከደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደግሞ አልፎ አልፎ የመቀነስ ሁኔታ ተስተዉሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በትግራይ እና በአማራ ክልል ሁሉም ዞኖች፤ ከሞላጎደል በሁሉም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ በወለጋ እና ሸዋ ዞኖች በጅማ እና በኢሉ አባቦራ፣ በጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ በሸካ፣ በከፋ፣ በጉራጌ እና ስልጤ፣ በወላይታ እና ጋሞጎፋ፣ በቤንች ማጂ፣ በሲዳማ፣ በአንዳንድ የአርሲ፣ ባሌ፣ ቦረና እና ጉጂ፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ እንዲሁም ከአፋር ክልል በዞን 01፣ 05 እና 03 ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአለም ከተማ 38.4፣ በአምባ ማሪያም 35.4፣ በአፅቢ 51.1፣ በአይደር 36.0፣ በቦሬ 47.0፣ በድሬዳዋ 34.2፣ በደባርቅ 43.0፣ በጋትራ 65.0፣ በጊምቢ 31.7፣ በጎሬ 33.4 እና 42.7፣ በካቺስ 37.3 እና 44.5፣ በላሊበላ 37.1፣ በሊሙገነት 42.0፣ በመሃልሜዳ 33.4፣ በማጀቴ 46.5፣ በማንኩሽ 34.8፣ በመተማ 37.8 እና 38.7፣ በማይፀብሪ 36.5፣ በሽሬ 50.3፣ በሲሪንቃ 38.6 እና 40.3፣ በሻሁራ 39.1፣ በሲርባአባያ 30.2፣ በወገልጤና 33.5፣ በአክሱም 41.0፣ በተርጫ 34.7፣ በቴፒ 34.8 እና 43.3፣ በጉንዶ መስቀል 45.4፣ በሶኬ 43.9፣ በወንበራ 35.1 እና በተንታ 41.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይ እና አማራ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከሞላጎደል በሁሉም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፣ በወለጋ እና ሸዋ ዞኖች፣ በጅማ እና በኢሉ አባቦራ፣ በሸካ፣ በከፋ፣ በጉራጌ እና ስልጤ፣ ከ50-153 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ6-10 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ በጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ በወላይታ እና ጋሞጎፋ፣ በሲዳማ፣ በአርሲ፣ ባሌ፣ ቦረና እና ጉጂ፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ እና ከአፋር ክልል በዞን 01፣ 05 እና 03 ላይም ከ5-46 ሚ.ሜ የደረሰ ዝናብ ከ2-5 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በትግራይ ክልል ዞኖች፣ በሰሜን እና ደቡብ ጎንደር፣ በሁሉም የአፋር ክልል ዞኖች፣ በሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ በጅማ እና ኢሉ አባቦራ፣ በከፋ እና ሸካ፣ በጉጂ እና ቦረና፣ በአንዳንድ የምዕራብ እና ምስራቅ ሀረርጌ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው። የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3)


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከኦገስት  1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት



ካርታ 3   እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# <u>እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

# <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ  አካባቢዎች ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ  ከላይ በተጠቀሱት የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ ተስተውሎ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ቀደም ሲል ከሰኔ ወር በፊት ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንደ ማሽላና በቆሎ የመሳሰሉት እንዲሁም ከሰኔ ወር በኋላ ተዘርተው በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉት  እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ ለመሳሰሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬ እህሎችና የቅባት እህሎች ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን፤ በአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ  ነበረዉ። ይሁን እንጂ ከክረምቱ ዝናብ መጠናከር ጋር ተያይዞ ከባድ ዝናብ የነበራቸው አካባቢዎች ነበሩ ከነዚህም መካከል በስሪንቃ በረዶና ነፋስ በቀላቀለ ከባድ ዝናብ በእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እና ቋሚ ተክሎች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት ሁኔታዉ በመጠኑ የመቀነስ ሁኔታ የነበረዉ ሲሆን፤ በግብርናዉ እንቅስቃሴ ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅእኖ አልንበረዉም (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4    እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# <u>እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ 1-10 ኦገስት 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በአገሪቱ ምዕራባዊ አጋማሽና በሰሜን የሀገሪቱ ክፌሎች በሚገኙ ዋና ዋና ተፋሰሶች እንዲሁም በመካከለኛው ከፍተኛ ቦታዎች ላይ የሚገኙ የላውላ፣ የአዋሽ፣ የስምጥሸለቆና የዋቢሸበሌ የላይኛው ክፍል ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ እንዲሁም አብዛኛው የአባይ፣ የባሮአኮቦ፣ የተከዜ፣ የኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የላይኛው አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢሸበሌና አፋር ደናክል ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል መካከለኛው ዋቢሸበሌና አፋርደናከል፣ የላይኛው ገናሌዳዋ፣ የአዋሽ ከፍተኛ ቦታዎች፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም ጥቂት የታችኛው ባሮአኮቦ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡

በመሆኑም ባለፉት አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ለውሃ ሃብት ከፍተኛ ግብዓት ከመሆኑም በላይ በመጠን ረገድ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በተከታታይ ከባድ ዝናብ በመኖሩ የወንዞች እና የውሃ ማጠራቀሚያዎች ከመደበኛው ወቅት ቀደም ብሎ የውሃ ሙላት ተከስቶባቸዋል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 11-20/2018 የሚኖረው
# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከሞላ ጎደል ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀዳሚው አሥር ቀናት በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው። አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተጠናከረ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በመሆኑም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜን ሸዋ በተጨማሪም የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ የትግራይ ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋ፣ የቤንች ማጂ፣ የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋና የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት መንስኤ ሊሆን ይችላል። ከዚህም ሌላ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ የአፋር ዞን 1፣ 3፣ 4 እና 5፤ የአርሲና ባሌ ዞኖች፣ የቦረናና የጉጂ እንዲሁም የጅጅጋና የሸንሌ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ህዝቦች ከቀላል እስከ መካከለኛው መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

# እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ
# በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በመጪው የኦገስት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ከቀዳሚው አሥር ቀናት በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአብዛኛዎቹ የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ በሚያከናውኑ አካባቢዎች እርጥበታማ ሁኔታው እንደሚጠናከር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ልዩልዩ የመኸር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ባለፉት አስር ቀናት የእርጥበት

እጥረት ለነበረባቸው የምስራቅና ደቡብ ምስራቅ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት ከማሻሻሉም በተጨማሪ የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ የእርጥበት እጥረት ለነበረባቸው ስፍራዎች የአዝዕርቱን የውሃ ፍላጎት መሟላትና የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ስለሆነ የሚመለከተዉ ክፍል የዉሃ መሰብሰብ ሥራዎችን ቢሠራ ዕጥረት በሚገጥምበት ጊዜ በአንዳንድ ማሣዎች ላይ ዉሃዉን ለመጠቀም ይረዳል። በሌላም በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ ከመፍጠሩ ጋር ተያይዞ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ላሉ ሰብሎች አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው የበዛውን ውሃ ከማሳ በማስወገድ የጎርፍ ውሃ መቀልበሻ ቦዮችን በመስራት ከወዲሁ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃርም ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና እንዲሁም በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር ለፀረ ሰብል ተባይ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ሰለሚችል የሚመለከተው ክፍል የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ ጥንቃቄ እንዲወስድ እንመክራለን፡፡ በአንፃሩ ደረቃማ ሊሆኑ እንደሚችሉ የተጠቀሱት አካባቢዎች ሊያገኙ የሚችሉትን መጠነኛ እርጥበት ከብክነት የመከላከል ተግባራትን ማከናወን ይጠበቃል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኦገስት 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስርት ቀናት ማለትም እ.ኤ.አ ከኦገስት 10-21/2018 ውስጥ በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ከፍተኛ የዝናብ መጠን የሚያገኙበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠን ሊኖር እንደሚችል ትንበያችን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አስር ቀናት በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሰው ላይ ሊኖር የሚችለውን ተፅዕኖ ስንመለከት በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች በተለይም የአባይ፣ የተከዜ፣ የባሮ አኮቦ፣ የላይኛውና መካከለኛው ኦሞ ጊቤና አዋሽ እንዲሁም የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም እርጥበታማ ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ጥቂት የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌና የኦጋደን ተፋሰሶች መጠነኛ የሆነ የዝናብ ስርጭት ሊኖር እንደሚችችል ትንበያችን ያመለክታል፡፡